# ትምህርተ ሃይማኖት



የሰው ልጅ ሰውኛውን ለመኖር ሲመጣ ባዶውን አልመጣም እሳተ ሕግ በልቡናው ተጻፍኖለት፣ የክፉና የበጐ መለያ ባህርይ በሰውነቱ ተሰማምቶት...ወዘተ. ነው።

በእግዚአብሔር ምሳሌ መፈጠሩም እንደ መላእክት ህያው ሆኖ በሕገ ልቡና ተገዝቶ ሊኖር እንጂ በመጽሐፍና በጸሐፊ፣ በትምህርትና በአስተማሪ ተደግፎ ሊኖር አልነበረም። በንጹህ ባህርዩ ጽንነት፣ ሁከትና ኃጢአት መንጭተው ሊአጠቁሩት አልነበረም፣ ንጹህ ባህርዩን ጠብቆ ከኖረ የግብር ጠላት የማይነሳበት ነፃ ፍጡር ነው።

በሥልጣንም የልጅነት (ልጅ የመሆን) ሥልጣን የተሰጠው፣ በገነት እንዲኖር የተፈቀደለት፣ ቅሩብ ኀበ እግዚኡ የሆነ ባለሟል ነበር። በሞት እንደ ቅጠል ሊረግፍ፣ በመሬት ጉያ ሊወተፍ አልነበረም። (ሄኖክ ፲፱፥፳፬) በምድረ ገነትም ሲኖር የሐልዮ፣ የነቢብና የገቢር ኃጢአት አልተገኘበትም። በንጽሐ ጠባይ ቢገኝ ኑሮ ማርጀት፣ መታመምና ሞት ሳያውቁት ሺህ ዘመን ሊመላው ግዘፉ ቀርቶ ርቀቱን ገንዘብ በማድረግ ከዓለመ ሥጋ ገነት ወደ ዓለመ ነፍስ መንግስተ ሰማይ ሊአርግ ነበር። በልቡናው የተጻፈለትን ሕግ በመተው ለጠላቱ ስለተረታ ሁሉንም አጥቶ ሞትና መቃብር ሲቀባበሉት ኖረ። ፈጣሪውንም ሰውን በመፍጠሩ እስኪአሳዝነው ድረስ ደረሰ። (ዘፍ.፫፥፳፪፤ ዘፍ.፮፥፮–፯) ይሁን እንጅ ሰው (አዳም) በአለ አእምሮ ነውና መውደቁን አወቀ፣ አቅሙን ተረዳ፣ ተጸጸተ ጸሎቱን (ልመናውን) ወደ ፈጣሪው አቀረበ። ቸር ይቅር ባይ ፈጣሪውም ልመናውን አይቶ፣ መጸጸቱን ተረድቶ፣ ይቅር ይለው ዘንድ ወሠነ። የውሣኔውንም ፍንጭ በእየጊዜ የሚናገሩ ነቢያት ተነሱ። (ኢሳ.፯፥፲፬፤ ዘጸ.፫፥፪፤ መሳ.፮፥፴፯፤ ዳን.፪፥፴፬) ለአባቶቻችን በነቢያት አድሮ ተናገረ። (ዕብ.፩፥፩) በሰማይ በምድር ያለው ሁሉ ይታደስ ዘንድ የሚታደስበት ጊዜ ሲደርስ ልጁን በሥጋ ላከው። (ኤፌ.፩፥፲፤ ገላት.፬፥፬) የአባቶቻችን ምኞት ሁሉ ህያው ሆነ። ሰውና እግዚአብሔር፣ ሰውና መላእክት፣ ነፍስና ሥጋ፣ ሕዝብና አሕዛብ አንድ ሆኑ። ቁራኝነት ጠፋ። የሰው መስዋዕቱ፣ ጸሎቱ፣ ልመናውና በጐ ሥራው ሁሉ ወደ ፈጣሪው ደረሰ። አምነው የሚጸልዩ ጸሎት ሁሉ ሰመረ። ድውይ ፈወሰ፣ ህሙም አዳነ (ያዕ.፭፥፲፭።)

## ሳታቋርጡ ጸልዩ

(ተሰሎ.፭፥፲፯–፳)

ይህ ይባል እንጂ አምነው የሚጸልዩት ጸሎት ሁሉ በእየጊዜው ግዳጅ ሲፈጽም፣ ችግርን ሲአስወግድ መኖሩ ግልጽ ነው። በጸሎቱ ጸሎተኛ በሃይማኖቱ ያፈረ ሃይማኖተኛ የለም። ነቢዩ ኤልያስ ልጅነት ባልተሰጠበት ጊዜ የነበረ አቢይ (ታላቅ) ነቢይ ነው። ይሁን እንጂ በጸለየው ጸሎትና በአቀረበው መስዋዕት አላፈረም። በሰዎቹ ክፋት አቅማቸውን ለማሳወቅ ዝናም ለዘር፣ ጠል ለመከር ከመስጠት እንዲከለከል አደረገ ሆነለትም። (፩ነገ.፲፯፥፩) አቅማቸውን ከአሳወቀ በኋላ ዝናም እንዲዘንም አደረገ። (፩ነገ.፲፰፥፵፪) ይህ ሁሉ እንዲፈጸም የሆነ በጸሎት ኃይል ነው፤ የጸሎትን ኃይል አድራጊነት ያስተምረናል፣ ጸሎት ለማኅበር፣ ለግለሰብእ...ወዘተ. ይጸለያል (ያዕ.፭፥፲፮።) በሃይማኖት ሆኖ ለወንድም የሚጸለየው ጸሎት ሁሉ እራስንም ይጠቅማል።

ጸሎት የሰውና የእግዚአብሔር መገናኛ ህቡዕ መሣሪያ ነው። (ማቴ.፮፥፮) ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ ስለተፈጠረ ከፈጣሪው ጋር መገናኘት አለበት። ጸሎት ሲባል የሰው በጐ ሥራዎች ሁሉ ጸሎት ይባላሉ። ለምሳሌ ስግደት፣ ምፅዋት፣ ትምህርት፣ ምስጋና ንስሐ:- የመሳሰሉት ሁሉ ጸሎት ይባላሉ። እነዳንኤል ከአፈ አንበሳ ሠለስቱ ደቂቅ ከእቶነ እሳት የዳኑ በጸሎት ነው። (ትንቢተ ዳንኤል ፫፥፳፬፤ ፮፥፳) በእየጊዜው ጾመ ድህነት እያልን የምንናገራቸው ጾሞች ለምሳሌ ጾመ ረቡዕና ጾመ አርብ ናቸው። እኒህም ሁለት ጾሞች በሁለቱ ቤቶች የተከናወኑ ድንቅ ተአምር ተደርጐ የተፈፀሙ ጾሞች ናቸው። (መጽሐፈ ዮዲት ፲፫፥፮፤ መጽሐፈ አስቴር ፯ና ፰ ተመልከት።) ጸሎት ከኃያል እግዚአብሔር ብርታትን ለማግኘት የምንጠይቅበት ልዩ ማመልከቻ ነው። የጸሎት ሥነ ሥርአትና ዝግጅት ይኑረው እንጂ ተፈጻሚነቱ በተሰበረ ልብ እና ትህትናን በተላበሰ ውስጣዊና ውጫዊ የተግባር ሚዛን ሲተካከል ነው። (ዮሐ.፬፥፳) በጸሎት ማንኛ



www.ethiopianorthodox.org

ውም ተግባር የምንፈጽም ሲሆን በጸሎት የማይፈጸምልን ውጤት እንደሌለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮናል (ሉቃ.፲፰፥፩።) ጸሎት ፍሬአማ የሚሆነው በሚከተለው መንገድ ሲቀርብ ነው። (ዕብራውያን ፲፩፥፮፤ ኤር.፰፥፫) ያለ ሃይማኖት መጸለይ ያለ ጸሎት አፈጻጸም እንደማይገኝ ብዙዎች መጻሕፍት ተባብረዋል። የጸሎታችንም ፍጻሜ ፈቃድህ ይሁን በማለት መሆን አለበት። ምክንያቱም ለእኛ ከእኛ እሱ ቀራቢ ስለሆነ ነው። (ማቴ.፮፥፲፬) ደግሞም በስልቹነት ባህርይ አይደለም። (ሉቃ.፲፩፥፰) በሕግ፣ በአምልኮት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቀድሞ ሊአምን ይገባል። በዕብራውያን መልእክት በ፲፩፥፮–፵ ቅዱስ ጳውሎስ የጠቀሳቸው ሁሉ አስገራሚ ሥራ የሠሩ በሃይማኖት እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ ያስረዳል። የጸሎትና የሃይማኖት ጥምረት ሊከሽፍ የማይችል መሣሪያ መሆኑ ማንኛውም ሰው ሊረዳ ይገባል።

የዘመናችን ትውልድ ያልሰጡትን በመሻቱ፣ የተሰጠውን እያጣ፣ ከሕግ ጥበቃ በመውጣቱ፣ ለጠላት እየተጋለጠ፣ የተሰጠውን የእድሜ ጣሪያ ሳያይ በከንቱ ከዓለም ሲሰናበት ይገኛል። ጸሎቱና እምነቱም ያልተጣጣመ በመሆኑ ለተለያዩ ችግር እጁን ሰጥቶ፣ አሳዛኝ አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ፣ ለችግር፣ ለርሃብ፣ ለእርዛት፣ ለድንቁርናና ለስደት ምርኮኛ ሆኖ ይገኛል። «የእሱን ነገር ለእርሱ መንገር» እንደ ተባለው በጥበበ እግዚአብሔር ሆኖ ተግሣፁን እየተቀበሉ መኖር ከእግዚአብሔር ቁጣና ከሰው ሰራሽ ችግር መዳን ይቻላል (መዝ.፬፥፲።) በሃይማኖት ሁነው (ጸንተው) የሚጠይቁት ሁሉ ነገ አገርን፣ ወገንን፣ ከልዩ ልዩ ችግር ያድናል መዝ.፵፱፥፲፭፤ ዮሐ.፫፥፰–፲። ለዚህ ደግሞ ሳያቋርጡ መጸለይ ይገባል (ተሰሎ.፭፥፲፯–፲፰) ✣

# እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ሩቅ ነው፣ ጥበቡ አይታይምና፤

እግዚአብሔር ቅርብ ነው፣ ቶሎ ይሰማልና፤

እግዚአብሔር መኰንን ነው፣ ቶሎ ይፈርዳልና፤

እግዚአብሔር እንግዳ ነው፣ ቶሎ ወሬ ይሰማልና፤

እግዚአብሔር ትሑት ነው፣ ሰውን አይንቅምና፤

እግዚአብሔር መሐሪ (ርኅሩኅ) ነው፣ ይቅር ይላልና፤

እግዚአብሔር ሐኪመ ነው፣ ሁሉን በጥበብ አድርጓልና፤

እግዚአብሔር ምስጉን ነው፣ ፀሐይን፣ ጨረቃን ፈጥሮአልና፤

እግዚአብሔር ክቡር ነው፣ ሰማይና ምድር የርሱ ናቸውና፤

እግዚአብሔር ባለጸጋ ነው፣ ለሁሉም ይመግባልና፤

እግዚአብሔር ረቂቅ ነው፣ አይጨበጥምና፤

እግዚአብሔር ግዙፍ ነው፣ በዓለሙ ሁሉ ሞልቷልና፤

እግዚአብሔር ብሩህ ነው፣ ጨለማ የለበትምና፤

እግዚአብሔር ኃያል ነው፣ የሚቋቋመው የለምና፤

እግዚአብሔር እሳት ነው፣ እጅግ ያስፈራልና፤

እግዚአብሔር መካር ነው፣ መጻሕፍትን ሰጥቶናልና፤

እግዚአብሔር አባት ነው፣ አሳድጎናልና፤

እግዚአብሔር ወንድም ነው፣ ሰው ሆኖዋልና፤

እግዚአብሔር ወዳጅ ነው፣ የሆዱን ነግሮናልና፤

እግዚአብሔር አገር ነው፣ እንኖርበታለንና፤

እግዚአብሔር ማርና ሱካር ነው፣ ይጣፍጣልና፤

እግዚአብሔር ገናና ነው፣ የሚያህለው የለምና፤

እግዚአብሔር ትልቅ ነው፣ ሰፍራ አይበቃውምና፤

እግዚአብሔር ጥልቅ ነው፣ በዋና አይገኝምና፤

እግዚአብሔር ፋሲካ ነው፣ ለሁሉ ታርዷልና፤

እግዚአብሔር ዓመት በዓል ነው፣ ለሁሉ ደስታ ነውና፤

እግዚአብሔር ጨው ነው፣ ሁሉን ያጣፍጣልና፤

እግዚአብሔር ክረምት ነው፣ ሁሉን ያበቅላልና፤

እግዚአብሔር አይጠረጠርም፣ ሁሉን ያውቃልና፤

እግዚአብሔር አይዘነጋመ፣ በሁሉም ድካም የለበትምና፤

እግዚአብሔር አይሰጋም፣ የሚሸረው የለምና፤

እግዚአብሔር የሰው ሎሌ ነው፣ በክረምት ለማብቀል በበጋ ለማብሰል የተዘጋጀ ነውና፤

እግዚአብሔር እንግዳ አይደለም፣ ከጥንት የነበረ ነውና

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ጥንት ለነበረ፣ አሁንም ላለ ኋላም ለሚኖር አሜን።

መጽሐፈ ጨዋታ – ሥጋዊ ወመንፈሳዊ

ከዘነበ ኢትዮጵያዊ – ፲፰፻፶፯ ዓ.ም



www.ethiopianorthodox.org